2023



MARYLAND STATE DEPARTMENT OF EDUCATION
EQUITY AND EXCELLENCE

**የወላጅ ተከታታይ መረጃ**
በ Maryland የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች፦

# የግለሰባዊ ትምህርት መርሃ-ግብር (IEP)

የልዩ ፍላጎት ትምህርት ሂደት
የወላጅ መብቶች
**IEPን መረዳት**
የሁለተኛ ደረጃ ሽግግር



# መግቢያ

**በ Maryland የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት የወላጅ መመሪያ፤ የ Maryland ከልደት እስከ 21 የወላጅ ተከታታይ መረጃ ክፍል ሲሆን፤  በሜሪላንድ የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት ስርዓት ውስጥ ቤተሰቦችን ለመደገፍ የተነደፈ የሕትመት ስብስብ ነው። ይህ ቡክሌት እያንዳንዱን የ IEP ክፍል ያብራራል፤ እናም ቤተሰቦች የልጃቸውን IEP ለማዳበር፣ ለመገምገም እና ለማሻሻል በሚደረገው ሂደት ሙሉ በሙሉ እንዲሳተፉ ያግዛል።**



# የማውጫ ሰንጠረዥ


ገጽ 4

**በልዩ ፍላጎት ትምህርት ሂደት ውስጥ የወላጅ ተሳትፎ**

ገጽ 5

**ህጉ ምን ይላል**

ገጽ 6

**የግለሰባዊ ትምህርት መርሃ-ግብር (IEP)**

ገጽ 16

**ለወላጆች የማረጋገጫ ዝርዝር**

ገጽ 18

**ጥያቄዎች ካሉኝ ወይም እርዳታ ቢያስፈልገኝስ?**


ለበለጠ መረጃ በዚህ ይጎብኙን

**www.marylandpublicschools.org**

## የወላጅ ተሳትፎ
# በልዩ ፍላጎት ትምህርት ሂደቱ ላይ



**ወላጆች በልጆቻቸው ትምህርት ላይ መሳተፋቸው የላቀ ስኬት ያስገኛል።** ይህ በተለይ ለልዩ ፍላጎት ትምህርት ብቁ ለሆኑ ልጆች የበለጠ አስፈላጊ ነው። ወላጆች በልጆቻቸው ትምህርት ለመሳተፍ፣ በትብብር ለመስራት እና ከትምህርት ቤቱ ጋር አጋር ለመሆን ትርጉም ያላቸው እድሎች ሲኖራቸው፣ የልዩ ፍላጎት ትምህርት የበለጠ ውጤታማ ይሆናል።

የልዩ ፍላጎት ትምህርትን የሚመራው ሕግ፤ የአካል ጉዳተኞች ትምህርት ሕግ (IDEA) አርቃቂዎች እንደፃፉት፣ "የአካል ጉዳተኛ ልጆች ትምህርት የበለጠ ውጤታማ ሊሆን የሚችለው ... የወላጆችን ሚና እና ኃላፊነት በማጠናከር እና ቤተሰቦች... በትምህርት ቤት እና በቤት ውስጥ በልጆቻቸው ትምህርት ውስጥ ለመሳተፍ፣ ትርጉም ያላቸው እድሎች እንዲኖራቸው በማድረግ ነው " (PL 108-446 (5) (B))። ወላጆች እና ቤተሰቦች በልጆቻቸው ትምህርት ውስጥ ንቁ አጋሮች መሆናቸው አስፈላጊ ነው።

በልዩ ፍላጎት ትምህርት ሂደት ውስጥ፤ ወላጆች ስለ ልጆቻቸው ትምህርት ውሳኔ የሚሰጠው ቡድን ተፈላጊ አባል ናቸው። ወላጆች ልጆቻቸውን በደንብ ያውቃሉ፤ እናም ለሌሎች የልጃቸው ቡድን አባላት የሚያጋሩት ጠቃሚ መረጃ አላቸው።

ቡድኑ "የተማሪውን ልዩ ፍላጎቶች" ለማሟላት እና በትምህርት ቤት ሁኔታ ውስጥ ስኬታማ እንዲሆን ለመርዳት የተነደፈ መርሃ-ግብር ለማዘጋጀት በጋራ ይሰራል።

# ህጉ ምን **ይላል**

## IEP ምንድን ነው?

**IEP፤ በ 34 CFR §§300.320-300.324 መሠረት በስብሰባ ላይ ተቀርጾ፣ ተገምግሞ እና ተሻሽሎ የአካል ጉዳተኛ ልጅን በተመለከተ የሚቀርብ የጽሁፍ መግለጫ ሲሆን ይህም የሚከተሉትን ማካተት አለበት፦**

- የልጁ ወቅታዊ የትምህርት ውጤት እና ተግባራዊ አፈፃፀም ደረጃዎች መግለጫ፤
- የትምህርት እና ተግባራዊ ግቦችን ጨምሮ መለካት የሚችሉ አመታዊ ግቦች መግለጫ፤
- ልጁ አመታዊ ግቦችን በማሳካት ረገድ የሚያደርገው እድገት እንዴት እንደሚለካ፤ እና ልጁ አመታዊ ግቦችን ለማሳካት እያደረገ ስላለው መሻሻል ወቅታዊ ሪፖርቶች መቼ እንደሚቀርቡ የሚገልጽ መግለጫ፤
- ለልጁ የሚሰጠው የልዩ ፍላጎት ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች እና ተጨማሪ እርዳታዎች እና አገልግሎቶች መግለጫ፣ እና የሚደረጉ የመርሃ-ግብር ማሻሻያዎች ወይም ለት/ቤት ሰራተኞች የሚቀርቡ ድጋፎች መግለጫ፤
- ልጁ በመደበኛ ክፍል ውስጥ አካል ጉዳተኛ ካልሆኑ ልጆች ጋር የማይካፈል ከሆነ፣ ካለ፣ የጉዳዩን ስፋት እና ለምን እንደሆነ የሚገልጽ ማብራሪያ፤
- የግለሰባዊ ተገቢ ማመቻቸቶች መግለጫ፤
- የ IEP ቡድን ልጁ ከመደበኛው ግምገማ ይልቅ በአማራጭ ግምገማ ውስጥ እንዲሳተፍ ከወሰነ፣ ግምገማው ለልጁ ለምን ተገቢ እንደሆነ የሚገልጽ መግለጫ፤
- ከ14 ዓመት ጀምሮ በየዓመቱ የሚሻሻሉ የሽግግር አገልግሎቶች፤ እና
- አቅመ-አዳም /አቅመ-ሄዋን ላይ ሲደርሱ የመብት ማስተላለፍ መግለጫ።

**ወላጅ ማን ነው? 34 CFR §300.30**

### ወላጅ ማለት

- የአንድ ልጅ ተፈጥሯዊ ወይም የጉዲፈቻ ወላጅ፤
- አሳዳጊ ወላጅ፤ የስቴት ህግ፣ ደንቦች፣ ወይም  ከስቴት ወይም ከአካባቢ የህግ አካል ጋር ያሉ የውል ግዴታዎች የአደራ አሳዳጊዎች እንደ ወላጅ እንዳይቆጠሩ ካልከለከሉ በስተቀር፤
- በአጠቃላይ የልጁ ወላጅ ሆኖ እንዲያገለግል ስልጣን የተሰጠው አሳዳጊ። ወይም ለልጁ ትምህርታዊ ውሳኔዎችን እንዲያደርግ የተፈቀደለት (ልጁ በስቴት ጥበቃ ስር ከሆነ፤ ስቴቱ መሆን አይችልም)፤
- ከልጁ ጋር አብረው የሚኖሩ (አያት፣ የእንጀራ ወላጅ፣ ወይም ሌላ ዘመድን ጨምሮ) ተፈጥሯዊ ወይም የጉዲፈቻ ወላጅን ተክቶ የሚሰራ ግለሰብ፤ ወይም ለልጁ ደህንነት ሀላፊነት ያለው ግለሰብ፤ ወይም
- በ §300.519 ወይም በህጉ አንቀጽ 639(a)(5) መሰረት የተሾመ ምትክ ወላጅ።

# የግለሰባዊ
# ትምህርት መርሃ-ግብር (IEP)

**የ Maryland የበይነመረብ IEP (MOIEP)፤ ከፌዴራል እና ከስቴት ደንቦች ጋር ወጥነት ያለው አፈፃፀምን ለማረጋገጥ፤ ለአካባቢ ትምህርት እና ለህዝብ ኤጀንሲዎች የቀረበ በየጊዜው የሚሻሻል መሳሪያ ነው።** በቅጾቹ ላይ ማሻሻያ ሲደረግ፤ ከማህበረሰብ አጋሮች እና የዘርፉ ባለሙያዎች ግብዓት ይፈለጋል። በመጀመሪያ እና ከሁሉ በፊት የ IEP ቤተሰብን ወዳድ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል!

## IEP ክፍል በክፍል

### የተማሪ እና የቤተሰብ መረጃ

በዚህ ገጽ ላይ ያለው መረጃ ትክክለኛ መሆኑ በጣም ወሳኝ ነው። ወላጆች በጥንቃቄ መመርመር እና አድራሻቸው፣ ኢሜይላቸው እና የስልክ ቁጥራቸው ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው። መረጃው ብዙውን ጊዜ ከሌሎች የትምህርት ቤቱ የመረጃ ቋቶች የሚመጣ ሲሆን፤ ሙሉ የስርዓት ማሻሻያ ሊፈልግ ይችላል።


የተማሪን የትምህርት ቤት መረጃ

ስም፦ ______ የመሀከል ስም ______ የአባት ስም፦ ______
አድራሻ፦ ______
ከተማ፦ ______ ስቴት፦ ______ ዚፕ ኮድ፦ ______
ክፍል፦ ______
ልዩ የተማሪ መታወቂያ ቁጥር (የስቴት)፦ ______
የተማሪ መታወቂያ ቁጥር (የውስጥ)፦ ______
የተወለዱበት ቀን፦ ☐☐•☐☐•☐☐☐☐ (ወወ•ቀቀ•አአአአ)
ዕድሜ፦ ______ ጾታ፦ ◯ ወንድ ◯ ሴት

የዘር ግንድ

ብሄር፡ሂስፓኒክ ወይም ላቲን ☐ አዎ ☐ አይ
☐ የህንድ አሜሪካዊያን ወይም የአላስካ ተወላጆች
☐ የሀዋይ ተወላጅ ወይም የሌላ ፓስፊክ አይስላንድ
☐ ኤሺያን
☐ ጥቁር ወይም አፍሪካ አሜሪካዊ
☐ ነጭ

ተማሪው እንደ እንግሊዝኛ ተማሪ ተለይቶዋል፦ ◯ አዎ ◯ አይ
የልጁ የትውልድ ቋንቋ፦ ______
የመኖሪያ አውራጃ፦ ______
የመኖሪያ ትምህርት ቤት፦ ______
የአገልግሎት አውራጃ፦ ______
የአገልግሎት ትምህርት ቤት፦ ______
ተማሪው ለድንገተኛ ጊዜ መውጫ የተወሰነ ድጋፍ (ፎችን) ይጠይቃልን? ◯ አዎ ◯ አይ
አዎ ከሆነ፣ የመውጫ ድጋፍ (ፎችን) እዚህ ይጥቀሱ፦ ______
የገንዘብ ኃላፊነት ያለበት ሥልጣን የትኛው ነው? ______
ተማሪው በስቴት ድርጅት እንክብካቤና አሳዳጊነት ሥር ነው ያለው? ◯ አዎ ◯ አይ
መልሱ አዎ ከሆነ ድርጅቱን ይጥቀሱ፦ ______
ተማሪው የወላጅ ወኪል ያስፈልገዋል? ◯ አዎ ◯ አይ
የወላጅ ምትክ ስም፦ ______ ምትክ ስልክ ቁጥር፦ ______

**ወላጅ/አሳዳጊ 1**
ስም፦ ______ የመሀከል ስም መጀመሪያው፦ ______ የአባት ስም፦ ______
የቤት ስልክ ቁጥር፦ ( ) - ______ ሴል ፎን፦ ( ) - ______
ኢሜል፦ ______
የወላጅ የትውልድ ቋንቋ፣ እንግሊዝኛ ካልሆነ፦ ______
አስተርጓሚ ያስፈልጋል? ◯ አዎ ◯ አይ

**ወላጅ/አሳዳጊ 2**
ስም፦ ______ የመሀከል ስም መጀመሪያው፦ ______ የአባት ስም፦ ______
የቤት ስልክ ቁጥር፦ ( ) - ______ ሴል ፎን፦ ( ) - ______
ኢሜል፦ ______
የወላጅ የትውልድ ቋንቋ፣ እንግሊዝኛ ካልሆነ፦ ______
አስተርጓሚ ያስፈልጋል? ◯ አዎ ◯ አይ

የፍይል አስተዳዳሪ፦ ______
የ IEP ቡድን ስብሰባ ቀን(ኖች)፦ ______
የ IEP ዓመታዊ ግምገማ ቀን፦ ______
◯ የሥርዓት መከላከያ የወላጅ መብቶች ሰነድ ለወላጅ ተሰጥቶትል/ተስጥቷትል።
◯ በአይኢፒ የቡድን ሂደት ውስጥ ወላጆች ያላቸውን መብቶችና ሃላፊነቶች በተመለከተ
◯ ለወላጆች የሃቢሊቴቲቭ አገልግሎቶችን በተመለከተ፣ የሜሪላንድ ኢpንሹራንስ አስተ
የቃልና የጽሁፍ ማብራሪያ ተሰጥቷቸዋል፡፡
የአፍ መፍቻ ቋንቋ ትርጉም፦ ወላጅ ተነግሮታ/ፖታል ◯ አዎ ◯ አይ ◯
የሚቀጥለው ዓመታዊ ግምገማ ቀን፦ ______
በቅርብ ግምገማ የተደረገበት ቀን፦ ______
ለግምገማ የታቀደው ቀን፦ ______
ዋና የአካል ጉዳት፦ ______
በአካል ጉዳት ምክንያት ተጽእኖ ያለባቸው ጉዳዮች፦ ______

መረጃዎን በጥንቃቄ ይመርምሩ። ትክክለኛነቱን ያረጋግጡ!



## የብቁነት መረጃ

የሚቀጥለው ክፍል በልጅዎ የመጀመሪያ እና ቀጣይነት ያለው የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ብቁነት ላይ ያተኩራል። የግምገማ የመጀመሪያ ስምምነት ቀኖች፣ የመጀመሪያ ብቁነት፣ የብቃት ምድብ እና የውሳኔው መሠረት የዚህ ክፍል አካል ነው። የልጅዎ ብቁነት ምድብ በዳግም ግምገማ ሊቀየር ይችላል።

በዚህ ክፍል ውስጥ ያለው መረጃ ሊለወጥ ይችላል። ለመረዳት ይህንን ክፍል ይከልሱ።

---

## በዲስትሪክት/በስቴት አቀፍ ምዘናዎች ላይ መሳተፍ እና የምርቃት መረጃ

ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ ወይም በመርሃ-ግብር ማጠናቀቂያ ምስክር ወረቀት ሊመረቁ ይችላሉ። የምረቃ መስፈርቶች፤ እንደ የ IEP ሂደት አካል፤ ለወላጆች በየአመቱ መገለጽ አለባቸው። ይህ አስፈላጊ የሆነበት ምክንያት፤ ተማሪዎች በየአመቱ በሚሳተፉበት የስቴት ምዘና አይነት፤ የተወሰኑ የመመረቂያ መስፈርቶችን የሚያሟሉ መሆን አለመሆናቸውን ስለሚያሳውቅ ነው። ተማሪዎች ዲፕሎማ (አማራጭ ምዘና በመባል ይታወቃል) እንዲያገኙ ላያስችላቸው በሚችል የስቴት ምዘና ላይ እንደሚሳተፉ የ IEP ቡድኑ ከወሰነ፤ የወላጅ ፈቃድ ያስፈልጋል። ስለዚህ ርዕስ የበለጠ መረጃ ለማግኘት፤ የቴክኒክ ድጋፍ ቡሌቲን 19-07፤ *ጉልህ የሆነ የግንዛቤ ችግር ላለባቸው ተማሪዎች ውጤቶችን ማሻሻል* እና 17-02፤ *በ Maryland ህግ መሰረት የወላጅ ፈቃድ*፤ ይመልከቱ።



ተማሪዎች በዲስትሪክት/በስቴት ምዘናዎች ላይ የሚኖራቸው ተሳትፎና የምርቃት መረጃ

**የምርቃት መስፈርቶች ለወላጆች ተብራርተዋል** ◯ አዎ ◯ አይ
የስቴት የምርቃት መስፈርቶች በሚከተለው ድረ ገጽ ሊገኙ ይችላሉ www.marylandpublicschools.org.
ማናቸውንም ተጨማሪ የአካባቢ የምርቃት መስፈርቶች ይመዝግቡ: ____________

**የታቀደ የመውጫ ምድብ፥**
ተማሪው የሚከተለውን ይዞ ይወጣል፥
◯ የሜሪላንድ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ
(ተገቢ የሆነውን ሁሉ ይምረጡ)
☐ የአሜሪካን የምልክት ቋንቋ ሊያካትት በሚችለው World Language በ2 ክሬዲት፣
☐ በ Advanced Technology በ2 ክሬዲት
☐ በስኬታማነት ከተጠናቀቀ በግዛት የተፈቀደ ስራ እና የቴክኒክ ትምህርት ፕሮግራም ጋር
◯ የፕሮግራም ማጠናቀቂያ ምስክር ወረቀት በትምህርት ዘመኑ መጨረሻ ተማሪው 21 ዓመት ይመላዋል
◯ ተማሪው ዕድሜው 21 ሲሆን የትምህርት ዓመቱ ሲያልቅ የመርሃ ግብር ፍጻሜ የምስክር ወረቀት (የወላጅና የተማሪ ምርጫ)

**የታቀደ የመዉጫ ጊዜ፦**
ተማሪዉ የ ____________ አመት ትምህርት እየተከታተለ ሲሆን በ ____________ (ወር.ቀን.አመት) ይመረቃል። መውጫ ላይ ተማሪው የትምህርት ውጤት፣ የተግባር አፈፃጸም፣ የማረፊያ ቤቶች እና ድህረ ሁለ
አፍ ፐርፎርማንስ (MSOP) ይቀበላል።

በአንቀፅ §8-412.1 የሜሪላንድ መመሪያ መሰረት ውስጥ እንደተገለጸው፣ በ IDEA ስር ያሉ መብቶች ውስን ከሆኑ ሁኔታዎች በስተቀር ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ለአቅመ አዳም ሲደርሱ እንደማይተላለፉ ለተማሪው እና ለ

**በአሁኑ IEP ላይ በሚሰጠው የ (MCAP) ፈተና ላይ በ ሜሪላንድ ሁሉን አቀፍ ምዘና ፕሮግራም ላይ ተሳትፎ ለማድረግ ያቅዱ**
ተማሪው ከ 3ተኛ እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ **በሜሪላንድ ሁሉን አቀፍ ፕሮግራም (MCAP)** ላይ ይፈተናል
**የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበቦች/ስነ ጽሁፍ** ◯ አዎ ◯ አይ ሂሳብ ◯ አዎ ◯ አይ ማህበራዊ ሳይንስ (8ኛ ክፍል ብቻ) ◯ አዎ ◯ አይ

ተማሪው በሜሪላንድ አጠቃላይ የምዘና ፕሮግራም (MCAP) **የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ በሚከተሉት** ምዘናዎች ላይ ይሳተፋል
የእንግሊዝኛ ቋንቋ የስነጥበብ/የትምህርት ◯ አዎ ◯ አይ አልጄብራ (Algebra) ◯ አዎ ◯ አይ ጂኦሜትሪ (Geometry) ◯ አዎ ◯ አይ መንግስት ◯ አዎ ◯ አይ

እነዚህ ሁሉ ልጅዎ ከትምህርት ቤት ከወጣ ከረጅም ጊዜ በኋላ ተጽእኖ የሚኖራቸው በጣም አስፈላጊ ውሳኔዎች ናቸው።

## ወቅታዊ የትምህርት ስኬት እና የተግባር አፈጻጸም (PLAFP) ደረጃዎች፦ ክፍል 1

የ PLAAFP ክፍል ለ IEP መሠረት ነው

ወቅታዊ የትምህርት ስኬት እና የተግባር አፈጻጸም ደረጃዎች (PLAFP) ለጠቅላላው IEP መሰረት ነው። ተማሪዎች ወዴት እንዲያመሩ እንደሚፈልጉ ለማወቅ፤ የት እንዳሉ ማወቅ አለብዎት። ይህ የ IEP ክፍል በተጠቀሰው ጉዳይ ላይ በመመስረት በርካታ የመረጃ ምንጮችን ይዟል። ጤና፣ ትምህርት፣ ማህበራዊ/ስሜታዊነት፣ ባህሪ፣ ንቃትን፣ መግባባትን፣ ሽግግር እና ሌሎች በትምህርት ቀን ውስጥ ሊሰራባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን ጨምሮ፤ ለእያንዳንዱ የተፅዕኖ ዘርፍ ክፍል መኖር አለበት። ከጤና PLAAFP በስተቀር በጤና እቅድ፣ በአገልግሎቶች ወይም መረጃ ሰጪ በመሆን ሊዳሰሱ የሚችሉ፤ ምክንያቱም የጤና ሁኔታ ተማሪዎች ላይ በትምህርት ቀን ተጽዕኖ ሊያሳድር የሚችል፤ ነገር ግን በመደበኛነት በትምህርት ቤት ውስጥ ሊታይ የማይችል፤ እያንዳንዱ የተፅዕኖ መስክ በግብ፣ በተጨማሪ እርዳታ እና በአገልግሎት፣ ወይም በ IEP ስምምነት ይስተናገዳል። ትምህርታዊ PLAAFPዎች የተማሪዎችን የክፍል ደረጃ አፈጻጸም ሁሉም የንባብ፣ የሒሳብ እና የጽሑፍ ቋንቋዎች ማዕቀፎችን ማካተት አለበት።

---

## ወቅታዊ የትምህርት ስኬት እና የተግባር አፈጻጸም ደረጃዎች፦ ክፍል 2

በዚህ ክፍል ውስጥ ሦስት ክፍሎች አሉ፦ (1) የወላጅ ግብአት፤ (2) የተማሪ ጥንካሬዎች፣ ፍላጎቶች፣ ግላዊ ስኬቶች እና ከትምህርት ቤት አካባቢ ውጭ ያሉ ባህሪዎች፤ እና (3) የተፅዕኖ መግለጫ። የወላጆች አስተያየት ሁል ጊዜ ከስብሰባው በፊት በጽሁፍ ይቀርባል፤ እናም በስብሰባው ወቅት መገምገም አለበት። ወላጆች በስብሰባው ወቅትም  አስተያየት ይሰጣሉ። ይህ ደግሞ በዚህ ክፍል ውስጥ መካተት አለበት።

የ IEP ቡድን አባላት ልጅዎን በተመለከተ ከትምህርት ውጭ ስላሉ ነገሮች ማወቃቸው አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ ከትምህርት ቤት ውጭ ምን ያደርጋሉ? ሽልማቶችን አሸንፈው ያውቃሉ? የተወሰነ የስፖርት ቡድን ይከተላሉ? የሽግግር እንቅስቃሴዎችን ሊመራ የሚችል ጠንካራ ፍላጎት አላቸው? ይህ ሁሉ ለማነቃቃት፣ በተጨማሪም ልጅዎን ለማወቅ እና ከእሱ ጋር ግንኙነት ለማዳበር ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል።

የተፅዕኖ መግለጫው አስፈላጊ የሆነ የ IEP አካል ነው። መግለጫው ሁሉን አቀፍ የሆነ እና በ PLAAFP ውስጥ ያለው መረጃ፤ የተማሪዎች አካል ጉዳት በክፍል ውስጥ እንዴት ተፅእኖ እንደሚያሳድርባቸው ማሳየት አለበት። ለምሳሌ፣ ተማሪዎች የሂሳብ ስሌት ላይ ችግር ካለባቸው፣ በሂሳብ ክፍል እና ምናልባትም በኬሚስትሪ እና ፊዚክስ ላይ፣ የሂሳብ እውነታዎችን በትክክል የማስላት ችሎታቸው ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል።

| ለትምህርት የደረሱ - አሁን ያላቸው የትምህርት ውጤትና የተግባር ብቃት |
|---|
| ስለ ተማሪው/ዋ የትምህርት መርሃ ግብር ወላጅ ያለው አስተያየት ምንድን ነው? (ትምህርታዊ፣ ተግባራዊ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ፣ ባህሪያዊ እና ሁለተኛ ደረጃ ሽግግርን ጨምሮ)<br>____________________<br>____________________<br>____________________<br>____________________<br>____________________<br>____________________ |
| የተማሪው ጠንካራ ጎን፣ ፍላጎት፣ ዋና የግል ባሕርዮች እና ብቃቶች ምንድን ናቸው/(ከትምህርት በኋላ ያሉ ውጤቶችን የሚመለከቱ ፍላጎቶችና ምርጫዎችን ጨምሮ፣ ተገቢ ከሆነ።)<br>____________________ |

የወላጅ ግብአት ለ IEP፤ ከስብሰባው በፊት እና በስብሰባው ወቅት ሊቀርብ ይችላል።

## የሁለተኛ ደረጃ የሽግግር አገልግሎቶች

አንድ ልጅ ትምህርት ከጀመረበት ቀን ጀምሮ ለሚቀጥለው ደረጃ ይዘጋጃል። ወይ ለኮሌጅ፣ ለሙያ ወይም ለማህበረሰብ፤ ተማሪዎች ከመጀመሪያ የትምህርት ቤት ዘመናቸው ጀምሮ የሚማሩት ነገር ሁሉ፤ የትኛውን መንገድ እንደሚመርጡ እና ከትምህርት ቤት ሲሸጋገሩ እንዴት እንደሚያበረክቱ ያዘጋጃቸዋል። በሜሪላንድ መደበኛ የሽግግር ሂደት የሚጀምረው በ14 ዓመት ነው። IEP ለሁለተኛ ደረጃ ሽግግር የተዘጋጁ በርካታ ክፍሎችን ያጠቃልላል፤ የተማሪ ምርጫዎች/ፍላጎቶች/ችሎታዎች፣ የሽግግር ተግባራት፣ ለጥናት የተዘጋጁ ትምህርቶች፣ የኤጀንሲ ትስስሮች። ለበለጠ ዝርዝር መረጃ እባክዎን የሁለተኛ ደረጃ ሽግግር የቤተሰብ መመሪያን ይመልከቱ።

## ልዩ ግምቶች

የልዩ ግምቶች ክፍል፤ የልጅዎን ትምህርታዊ መርሃ-ግብር በርካታ ወሳኝ አካላትን ይመዘግባል።

- የግንኙነት ፍላጎቶች፤
- የአጋዥ የቴክኖሎጂ ፍላጎቶች፤
- አይነስውር ለሆኑ ወይም የማየት ችግር ላለባቸው ተማሪዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች፤
- መስማት ለተሳናቸው ወይም የመስማት ችግር ላለባቸው ተማሪዎች የሚሰጡ አገልግሎት፤
- ጥብቅ ቁጥጥርን ወይም መገለልን ጥቅም ላይ ማዋልን ጨምሮ የባህሪ ፍላጎቶች፤ እና
- እንግሊዝኛ ተማሪ ለሆኑ ተማሪዎች የሚሰጡ አገልግሎቶች።





**መግባባት** (አስፈላጊ)

የተማሪው የአካል ጉዳት መግባባቱ ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል? ◯አዎ ◯አይ

(አዎ ከሆነ፤ የመግባባት ፍላጎቶች በ IEP ውስጥ እንዴት እንደሚፈቱ በአጭሩ ይግለጹ።) ______

ተማሪው አስተማማኝ የሆነ የመገናኛ ዘዴ (ለምሳሌ፤ የንግግር፣ የምልክት ቋንቋ፣ አበልጻጊ መግባቢያ) አለው? ◯አዎ ◯አይ

(አይ ከሆነ፤ ውጤታማ መግባባትን ለመፍጠር የሚቀርቡትን ግቦች፣ አገልግሎቶች ወይም ሌሎች ድጋፎችን ይግለጹ።) ______

**ረዳት ቴክኖሎጂ (AT)** (አስፈላጊ)

የአካል ጉዳት ያለበት ተማሪ የተግባራዊ አሠራር ችሎታውን ለማሻሻል፣ ለመቀጠል ወይም ለመጨመር የሚያስፈልጉትን የAT መሣሪያ(ዎች)ና አገልግሎት(ቶች)ን ይመልከቱ።

| ውሳኔ(ዎች)፡- | የ AT መሳሪያ(ዎች) ያስፈልገዋል/ያስፈልጋታል | |
|---|---|---|
| ◯ተማሪው AT መሳሪያ(ዎች) ወይም AT አገልግሎት(ቶች) አይፈልግም። | አይ | |
| ◯ተማሪው AT መሳሪያ(ዎች)ን አይፈልግም ነገር ግን AT አገልግሎት(ቶች)ን ይፈልጋል። | አይ | ተጨማሪ መ |
| ◯ተማሪው AT መሳሪያ(ዎች) እና AT አገልግሎት(ቶች) ይፈልጋል። | አዎ | አገልግሎቶች የሚያስፈ የውሂብ መስ |
| ◯ተማሪው AT መሳሪያ(ዎች) ን ይፈልጋል ነገር ግን AT አገልግሎት(ቶች)ን አይፈልግም። | አዎ | |

ለይቶ አግልግሎት መስጠት፤ የሕዝብ ባልሆኑ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለተመደቡ ተማሪዎች፤ በጣም ልዩ በሆኑ ሁኔታዎች ብቻ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል።



## የትምህርት አሰጣጥ እና መመዘኛ አቅርቦት ይዘቶች

ይህ የ IEP ክፍል በርካታ ንዑስ ክፍሎች አሉት። በመጀመሪያ፣ ለሁሉም ተማሪዎች የሚቀርቡ የተደራሽነት ይዘቶች አሉ። IEP ላላቸው ተማሪዎች ግን፣ ይዘቶቹ የ IEP አካል ከሆኑ መገኘት ብቻ ሳይሆን መቅረብ አለባቸው። ስለዚህ፣ የ IEP ቡድን እያንዳንዳቸውን ግምት ውስጥ ማስገባት እና የተማሪዎች የትምህርት መርሃ-ግብር አስፈላጊ አካል መሆናቸውን መወሰን አለበት። ተማሪዎችን እና ሰራተኞችን ለማዘጋጀት አንዳንድ የተደራሽነት ይዘቶች አስቀድመው ተለይተው መታወቅ አለባቸው።

የሚቀጥለው ንዑስ ክፍል የ IEP ወይም የክፍል 504 እቅድ ላላቸው ተማሪዎች ብቻ የሚያገለግሉ የአቀራረብ ማመቻቸቶችን ይዟል። እነዚህ ማመቻቸቶች በተማሪው PLAAFP ውስጥ በተንፀባረቁ ፍላጎቶች መደገፍ አለባቸው፤ እናም በትምህርት አሰጣጥ፣ በክፍል ምዘናዎች እና ግምገማዎች ላይ ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው።

የሚቀጥለው ንዑስ ክፍል የ IEP ወይም የ ክፍል 504 እቅድ ላላቸው ተማሪዎች ብቻ የሚያገለግሉ የምላሽ ማመቻቸቶችን ይዟል። ከእነዚህ ማመቻቸቶች የተወሰኑት በ IEP ውስጥ መቼ ሊካተቱ እንደሚችሉ ጥብቅ መስፈርቶች አሏቸው። ለምሳሌ፣ በምዘና ስሌት ክፍል ላይ ያለ የስሌት መሳሪያ፤ ወይም የማንበብ እና መጻፍ ምዘና ላይ ያለ የሰው አንባቢ። እነዚህ ማመቻቸቶች በተማሪው PLAAFP ውስጥ በተንፀባረቁ ፍላጎቶች መደገፍ አለባቸው፤ እናም በትምህርት አሰጣጥ፣ በክፍል ምዘናዎች እና ግምገማዎች ላይ ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው።

የመጨረሻው ንዑስ ክፍል የጊዜ ማመቻቸቶችን ይዟል። እነዚህ ማመቻቸቶች በተማሪው PLAAFP ውስጥ በተንፀባረቁ ፍላጎቶች መደገፍ አለባቸው፤ እናም በትምህርት አሰጣጥ፣ በክፍል ምዘናዎች እና ግምገማዎች ላይ ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው።

አንዳንድ የማመቻቸት ቃላቶች ግልጽ ላይሆኑ ወይም በትክክል እርስዎ የሚያስቡትን ትርጉም ላይሰጡ ይችላሉ። እርግጠኛ ለመሆን ማብራሪያ ይጠይቁ።

ያስታውሱ፦ እነዚህ ድጋፎች በትምህርት አሰጣጥ እና በግምገማ ወቅት ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው።

## ተጨማሪ እርዳታዎች፣ አገልግሎቶች፣ የመርሃ-ግብር ማሻሻያዎች እና ድጋፎች

ይህ የ IEP ክፍል የልዩ ፍላጎት ትምህርት አሰጣጥ መሰረታዊ ክፍሎችን ያካትታል። የተማሪዎን ልዩ ፍላጎቶች ለማሟላት የትምህርት አሰጣጥ የሚሻሻለው እዚህ ነው። በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉት ድጋፎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

- የትምህርት አሰጣጥ ድጋፎች፤
- የመርሃ-ግብር ማሻሻያዎች፤
- የማህበራዊ/የባህሪ ድጋፎች፤
- አካላዊ/አካባቢያዊ ድጋፎች፤ እና
- የትምህርት ቤት ሰራተኞች/የወላጅ ድጋፎች።

ለእያንዳንዱ ተጨማሪ ዕርዳታ፣ አገልግሎት፣ የመርሃ-ግብር ማሻሻያ እና ድጋፍ፤ ቡድኑ የሚተገበርበትን ቦታ እና እንዴት እንደሚተገበር በመግለጽ መለየት አለበት። ለትምህርት ቤት ሰራተኞች/የወላጅ ድጋፎች ክፍል፤ ተጨማሪ መረጃ ያስፈልጋል።

ይህ ክፍል ቡድኑ የአተገባበሩን ድግግሞሽ፣ የአገልግሎት አቅራቢዎችን እና የድጋፎችን ቆይታ እንዲወስን ይጠይቃል።

ሽግግሩ፣ የተደራሽነት ሁኔታዎችን፣ ተጨማሪ እርዳታዎችን፣ አገልግሎቶችን፣ የመርሃ-ግብር ማሻሻያዎች እና ድጋፎችን፣ ግቦች እና አገልግሎቶችን፣ በተራዘመ ትምህርት ቤት መዘጋት ወቅት ተግባራዊ የሚሆኑ ዝግጅቶችን ያካትታል።



> ወላጆች የራዕያቸውን መግለጫ ሲያካፍሉ፤ ስለ ልጆች የወደፊት ተስፋ የግል መረጃን እንዲያካፍሉ እድል ይፈጥርላቸዋል። ይህ መረጃ ጠቃሚ ግንዛቤን ይሰጣል እና የ IEP ቡድኑን ተማሪዎች ከምርመራ ወይም መጠሪያ ባሻገር እንዲመለከቷቸው ያስችላል።
>
> — Wendy Taylor



## የተራዘመ የትምህርት ዓመት

ለተራዘመ የትምህርት ዘመን (ESY) አገልግሎቶች፤ ሁሉም ተማሪዎች ብቁ አይደሉም። ESY የበጋ ትምህርት ቤት አይደለም፤ እናም ተማሪዎች በ ESY አገልግሎቶች ወቅት የውጤት ነጥብ አያገኙም። ለ ESY ብቁ የሆኑ ተማሪዎች በሚቀጥለው የትምህርት ዘመን እድገታቸው አደጋ ላይ የሚወድቅ ከሆነ፤ ይህም የሆነው በያዝነው የትምህርት ዘመን በተከሰቱት የእረፍት ጊዜያት በታየ ጉልህ የሆነ የብቃት መቀነስ ምክንያት እድገታቸው አደጋ ላይ ከወደቀ እና ተማሪዎች ከእረፍት ጊዜያት በፊት ወደነበሩበት ለመመለስ በሚፈጅባቸው ጊዜ ምክንያት ነው። ለ ESY ብቁነት በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ነው። የ IEP ቡድን ተማሪዎ ለአገልግሎቶች ብቁ መሆኑን ይወስናል። የ ESY ግብ ክህሎቶችን ማስቀጠል እንጂ ማሳደግ አይደለም፣ ስለሆነም የሚቀጥለው የትምህርት ዘመን ሲጀመር ተማሪው አሁን ባለው ችሎታ ላይ መገንባት እንዲችል ነው።

**የተራዘመ የትምህርት ዓመት (ESY)**

ተማሪው የESY አገልግሎቶች የማያገኝ ከሆነ፣ ከዚህ በታች ያሉት ሁኔታዎች ተማሪው ከመርሃ ግብሩ የሚያገኛቸው ጥቅማጥቅሞች ይቀሩበት እንደሆነ የ IEP ቡድን መወሰን አለበት። የESY አገልግሎቶች በግል የሚሰጡ የልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች ቅጥያ ሲሆኑ፣ የመንግሥት ድርጅቱ ከወሰነው መደበኛ የትምህርት ዓመት ባሻገር በ IEPው መሠረትና ለወላጅ ምንም ወጪ ሳያስወጡ የሚሰጡ ናቸው።

◯ የESY ውሳኔ ለሌላ ጊዜ ተላለፈ

**ESY በተመለከተ ሲሆን፣ መልስዎ አዎ ወይም አይ ይሁን፣ ውሳኔውንም ይመዝግቡ፦**

1. የተማሪው/ዋ IEP ከዋነኛ ሕይወት ስልቶች ጋር የተያያዙ ዓመታዊ ዓላማዎችን ያጠቃልላሉ? ◯ አዎ ◯ አይ

   ውሳኔውን ለመደገፍ የሚደረግ ውይይት፦ ______________________

   1ሀ. በእረፍት ጊዜ እነዚህን ዋነኛ የሕይወት ስልቶችን በከፍተኛ የማጣት ወይም ወኋላ የመመለስ እና በተገቢ ጊዜ ውስጥ እነዚህን ስልቶች መልሶ ያለማግኘት ዕድል አለ? ◯ አዎ ◯ አይ

   ውሳኔውን ለመደገፍ የሚደረግ ውይይት፦ ______________________

   1ለ. ዋነኛ የሕይወት ስልቶች ጋር በተያያዘ የ IEP ዓላማዎችን በጥሩ የማከናወን ምልክቶች ተማሪው እያሳየ ነው? ◯ አዎ ◯ አይ

   ውሳኔውን ለመደገፍ የሚደረግ ውይይት፦ ______________________

2. አዲስ የሚታዩ ችሎታዎች ወይም የመሻሻል ዕድሎች ይታያሉ? ◯ አዎ ◯ አይ

   ውሳኔውን ለመደገፍ የሚደረግ ውይይት፦ ______________________

3. ትልቅ እንቅፋት የሆኑ አኳኋኖች አሉ? ◯ አዎ ◯ አይ

   ውሳኔውን ለመደገፍ የሚደረግ ውይይት፦ ______________________

ለተራዘመ የትምህርት ዘመን አገልግሎት ብቁነት በ IEP ቡድን የሚከናወን በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ነው።

## አመታዊ ግቦች

አመታዊ ግቦች በ PLAAFP ውስጥ ተለይተው በተቀመጡት የተማሪ ፍላጎቶች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። ግቦች ተማሪዎች በአፈፃፀማቸው እና በክፍል ደረጃቸው መካከል ያለውን ልዩነት ማጥበብ እንዲችሉ የሚያደርጉ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ጉዳዮች ናቸው። ግቦች ግለሰባዊ ናቸው፤ እና 5 ክፍሎችን ያካትታሉ፦ (1) ግቡ የሚፈጸምበትና የሚለካባቸው ሁኔታዎች፤ (2) የሚለካው ድርጊት ወይም ባህሪ፤ (3) ግቦቹ የሚከናወኑበት የጊዜ ገደብ፤ (4) የመለኪያ ዘዴ፤ እና (5) ችሎታን የማሳያ መስፈርቶች። እያንዳንዱ ግብ እነዚህን ክፍሎች የሚያካትቱ የዓላማዎች ስብስብን ያካትታል። የ IEP ቡድን በዓመታዊ ግቦች ላይ የታዩ መሻሻሎች፤ ለቤተሰቡ በየምን ምን ያህል ጊዜ ሪፖርት እንደሚደረግ ይወስናል። ተማሪው በውጤት መስጫ ጊዜ ውስጥ ግቡን ለማሳካት በቂ መሻሻል ካላሳየ፣ የ IEP ቡድን በተማሪው እድገት ላይ የትኞቹ ነገሮች ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ለመወያየት እና እንደ አስፈላጊነቱ በግቡ ወይም በተማሪዎች የትምህርት መርሃ-ግብር ላይ አስፈላጊውን ማስተካከያ ለማድረግ መገናኘት አለበት። በዓላማዎች ላይ መሻሻል አስፈላጊ ነው፤ ሆኖም ግን ለቤተሰቡ ሪፖርት የሚደረገው በዓመታዊ ግቦች ላይ ብቻ ነው።

ተማሪው አመታዊ ግብ ላይ ለመድረስ በቂ እድገት ካላደረገ የ IEP ቡድን መሰብሰብ አለበት።  ወላጆች ተማሪያቸው በሚፈለገው መስመር ላይ መሆኑን ለማረጋገጥ የሂደቱን ሪፖርቶች በጥንቃቄ መገምገም አለባቸው።


ዓላማ ________________________ ይህ ግብ የድህረ ሁለተኛ ደረጃ የሽግግር ግብን ይደግፋል? ከሆነ፣ እባክዎ ይለዩ፥ ☐ የስራ ቅጥር ☐ ትምህርት ☐ ስልጠና ☐ እራስን ች

ዓላማ፡- ሁኔታን ፣ ባህሪን ፣ የግዜ ገደብ፣ የልኬት ዘዴ እና ቅድመ ሁኔታን ያካተተ ________________________

የግዜ ገደብ - በ ☐☐•☐☐•☐☐☐☐ (ወወ•ቀቀ•አአአአ)

የልኬት ዘዴ(የሚመለከተዉን ሁሉ ይምረጡ) ☐ ኤሌክትሮኒክ ጽሁፉ አሠራሮች (የተጥቀመው መሳሪያ/ዘዴ)____ ☐ በክፍል ውስጥ የተመሠረተ ግምገማ (የተጥቀመው መሳሪያ/ዘዴ)____ ☐ የማስተዋል መዝገብ ☐ መደበኛ ግምገማ (የተጥቀመው መሳሪያ/ዘዴ)____ ☐ ፖርትፎሊዮ ግምገማ ☐ ሌላ ____

ቅድመ ሁኔታ(ችሎታ እና ይዞ ማቆየት) ከ ____ ☐ % ትክክለኛነት ☐ % ቅንሳ ☐ ____ ከ ____ ሙከራዎች ☐ % ጭመራ ☐ ሌላ____

የESY ዓላማ? ◯አዎ ◯አይ

ለ 10 ወይም ከዚያ በላይ ቀናት ትምህርት ቤቱ አካላዊ መዘጋትን በሚያስከትሉ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታዎች የመማሪያ እና የግምገማ ማመቻቸት እንደተፃፈ ሊተገበር ይችላል?
◯ አዎ ◯ አይ አይ ከሆነ ፣ አሁን ባለው የመማሪያ እና የግምገማ ማመቻቸት የሚያስፈልጉትን ለውጦች ይግለጹ ፦____

ዓላማ ቁ 1፡- ሁኔታን ፣ ባህሪን ፣ የግዜ ገደብ፣ የልኬት ዘዴ እና ቅድመ ሁኔታን ያካተተ____ ዓላማ ቁ 3፡- ሁኔታን ፣ ባህሪን ፣ የግዜ ገደብ፣ የልኬት ዘዴ እና ቅድመ ሁኔታን ያካተተ____

የ IEP ቡድኖች ለተማሪዎች ከፍ ያለ ግምት ሊኖራቸው ይገባል፤ እናም ተማሪዎች ትርጉም ያለው እድገት እንዲኖራቸው፤ በበቂ ሁኔታ የሚያጓጉ እና የሚያነሳሱ ግቦችን መፍጠር አለባቸው።



## አገልግሎቶች

ልጅዎ የሚያገኘው በልዩ ሁኔታ የተነደፈው የትምህርት አሰጣጥ እና ተዛማጅ አገልግሎቶች የሚመሩት በልጅዎ PLAAFPs አማካኝነት ነው።

ነፃ ተገቢ የህዝብ ትምህርት (FAPE) ለመቀበል፤ በልዩ ሁኔታ የተነደፈ የትምህርት አሰጣጥን እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን ጨምሮ፤ ተማሪዎ የሚያስፈልገውን አገልግሎቶች ቡድኑ ይወስናል። አገልግሎቶች በአጠቃላይ የትምህርት መቼት ውስጥ ወይም በተለየ መቼት ውስጥ ሊሰጡ ይችላሉ። የልዩ ፍላጎት አስተማሪ፣ አጠቃላይ አስተማሪ፣ የትምህርት አሰጣጥ ረዳት፣ ሌላ የተዛማጅ አገልግሎት አቅራቢ ግለሰብ ወይም የሰራተኞች ጥምር እና የአገልግሎቶቹን ቆይታ፣ እነዚህን አገልግሎቶች ማን እንደሚያቀርብ ቡድኑ ይወስናል።

## አነስተኛ ገዳቢ አካባቢ

ከ IDEA ተልዕኮዎች ውስጥ አንዱ፤ ተማሪዎች በተቻለ መጠን የአካል ጉዳተኛ ካልሆኑ እኩዮቻቸው ጋር አብረው እንዲማሩ ማድረግ ነው። ይህ አነስተኛ ገዳቢ አካባቢ (LRE) ውስጥ መሆን ይባላል። አካታች በሆነ ሁኔታ ውስጥ መማር፤ ለሁሉም ተማሪዎች በርካታ ጥቅሞች እንደሚያስገኝ በጥናት ተረጋግጧል።

ጥቅሞቹ ማህበራዊ፣ ትምህርታዊ፣ ስሜታዊ፣ አካላዊ፣ ባህሪያዊ እና ሌሎች አዎንታዊ ተፅእኖዎች ሊሆኑ ይችላሉ። ማካተት ሁሉም ተማሪዎች እንዲያድጉ ይረዳል። የ IEP ቡድን ተማሪዎች ለማንኛውም ያህል ጊዜ ከአጠቃላይ የትምህርት ሁኔታ መወገድ እንዳለባቸው ከወሰነ፤ ያንን ውሳኔ ማስረዳት እና በማስወገዱ ምክንያት በተማሪዎች ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለባቸው። ተማሪውን ከጠቅላላ የትምህርት መስክ ለማውጣት የሚወሰነው ውሳኔ የሚመራው በተማሪው ፍላጐቶች ላይ ነው፣ ይህም በ PLAAFP ውስጥ ተንጸባርቋል።



**ከሁሉ በታች ገደብ የሌለው አካባቢ (LRE) ውሳኔ ማድረጊያና ምደባ ባጭሩ**

አጠቃላይ የትምህርት ገበታው መሻሻል ስለሚያስፈልገው ብቻ የአካል ጉዳት ያለበት ተማሪ ለዕድሜው ተገቢ ከሆነ አጠቃላይ የትምህርት ገበታ አይነሳም።

እያንዳንዱ የህዝብ ወኪል ድርጅት የሚከተሉትን ማረጋገጥ አለበት፦

(i) የአካል ጉዳተኛ ልጆች፣ በሕዝብ ወይም በግል ተቋማት ወይም በሌሎች የእንክብካቤ መስጫ ተቋማት ውስጥ ያሉ ሕጻናትን ጨምሮ፤ በተቻለ መጠን የአካል ጉዳተኛ ካልሆኑ ልጆች ጋር ይማራሉ፤ እና

(ii) የአካል ጉዳተኛ ልጆችን ከመደበኛው የትምህርት አካባቢ፤ ወደ ልዩ መማሪያ ክፍሎች፣ የተለየ ትምህርት ወይም ሌላ ማዛወር የሚሆነው፤ የአካል ጉዳተኝነቱ ዓይነት ወይም ከባድነት በመደበኛ ክፍሎች ውስጥ ተጨማሪ እርዳታዎችን ... በአጥጋቢ ሁኔታ ማሳካት የማይቻል ከሆነ ብቻ ነው።

34 CFR § 300.114

በ IEP ቡድን ግምት ውስጥ የሚገቡትን ሁሉንም የምደባ አማራጮች ይዘርዝሩ። ______

የተመረጠውን የምደባ ምርጫ ያመልክቱ። ______

የተመረጠውን ትንሹን ገዳቢ አካባቢን (LRE) ያመልክቱ።

◯ የልዩ ትምህርት ምደባ (መዋእለ ህጻናት እድሜ 3-5)፦

- ☐ መደበኛ የሆነ የህጻንነት ፕሮግራምን ቢያንስ በሳምንት ለ 10 ሰዓታት መከታተልና በዚያ ሁኔታ ውስጥ አብዛኛውን ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች መቀበል
- ☐ መደበኛ የሆነ የህጻንነት ፕሮግራምን ቢያንስ በሳምንት ለ 10 ሰዓታት መከታተልና በሌላ ቦታ ውስጥ አብዛኛውን ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች መቀበል
- ☐ መደበኛ የሆነ የህጻንነት ፕሮግራምን በሳምንት ከ 10 ሰዓታት ባነሰ መከታተልና በዚያ ሁኔታ ውስጥ አብዛኛውን ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች መቀበል
- ☐ መደበኛ የሆነ የህጻንነት ፕሮግራምን በሳምንት ከ 10 ሰዓታት ባነሰ መከታተልና በሌላ ቦታ ውስጥ አብዛኛውን ልዩ ትምህርትና ተዛማጅ አገልግሎቶች መቀበል

☐ የአገልግሎት ሰጪ መገኛ ☐ የተለየ ክፍል ☐ የግል የተለየ የቀን ትምህርት ቤት ☐ የግል መኖሪያ ተቋም

☐ ቤት ☐ የህዝብ የተለየ የቀን ትምህርት ቤት ☐ የህዝብ መኖሪያ ተቋም

◯ የልዩ ትምህርት ምደባ (ክፍል K-21)፦

{ የትምህርት ሳምንት ውስጥ አጠቃላይ ጊዜ፦ ____ ሰዓቶች ____ ደቂቃ/ሳምንት } – { ከአጠቃላይ ትምህርት ውጪ አጠቃላይ ሰዓት፦ ____ ሰዓቶች ____ ደቂቃ/ሳምንት } = { አጠቃላይ ትምህርት ውስጥ አጠቃላይ ሰዓት፦ ____ ሰዓቶች ____ ደቂቃ/ሳምንት }

አማካኝ____ % በቀን

☐ የውስጥ አጠቃላይ ትምህርት(80% ወይንም ከዛ በላይ) ☐ የህዝብ ሆኖ የተለየ የቀን ትምህርት ቤት ☐ የግል ሆኖ የተለየ የቀን ትምህርት ቤት ☐ በቤተሰብ የተመደበ የግል ትምህር...

☐ የውስጥ አጠቃላይ ትምህርት(40% - 79%) ☐ የተለየ የግል የቀን ትምህርት ቤት ☐ ቤትለቤት ሆስፒታል

☐ የውስጥ አቃላይ ትምህርት(ከ 40% በታች) ☐ የህዝብ መኖሪያ አቅርቦቶች ☐ የሚሻሻሉ አቅርቦቶች

ከአጠቃላይ ትምህርት ገበታ ከተነሳ፣ አገልግሎቶቹ አጠቃላይ የትምህርት ገበታው ላይ ተጨማሪ እርዳታዎችና አገልግሎቶችን በመጠቀም ሊሰጡበት የማይችሉበትን ምክንያቶች ያብራሩ፦ ______

ተማሪው አካል ጉዳተኛ ካልሆኑ እኩዮቹ ጋር በትምህርታዊ፣ ትምህርታዊ ባልሆኑ እና ከመደበኛ ትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎች የማይሳተፍባቸውን የተወሰኑ ጊዜያት/ተግባራትን ያመልክቱ ወይም የቀኑ 100% ከተካተተ N...

☐ NA (የቀኑ 100% ተካቷል) ______

LRE በሚመርጡበት ጊዜ ተማሪውን ሊጎዱ የሚችሉ ጉዳዮች ወይም የሚያስፈልጉት/የሚያስፈልጓት አገልግሎቶች ጥራት ላይ የሚያመጣ ተጽእኖ አለ? ◯ አዎ ◯ አይ

MSDE የሁሉንም ተማሪዎች የተናጠል ፍላጎቶች ለማሟላት የተሟላ ቀጣይነት ያላቸው የትምህርት አካባቢዎችን ይደግፋል።

የተማሪዎን IEP ማንኛውንም ክፍል ለመረዳት እርዳታ ካስፈለግዎት፤ የቤተሰብ ድጋፍ ቡድንን በ 410-767-0255 ያናግሩ።





# **የቃላት** መፍቻ

**የተደራሽነት ይዘቶች**
በትምህርት እና ምዘና ወቅት ለሁሉም ተማሪዎች የሚቀርቡ ድጋፎች፣ ግን በ IEP ውስጥ ሲካተቱ ለተማሪው መሰጠት አለባቸው።

**የተራዘመ የትምህርት ዘመን (ESY)**
ከመደበኛው የትምህርት ዘመን ወይም ቀን በላይ የሚቀርቡ አገልግሎቶች ተማሪዎች ክህሎቶችን እንዲጠብቁ እና ለቀጣዩ የትምህርት ዘመን እድገታቸውን አደጋ ላይ የሚጥል ጉልህ የሆነ የብቃት መቀነስ እንዳይከሰት ይከላከላል።

**ነፃ ተገቢ የሕዝብ ትምህርት (FAPE)**
ለልዩ ፍላጎት ትምህርት ብቁ የሆኑ ልጆች፤ ነፃ ተገቢ የሕዝብ ትምህርት የማግኘት መብት አላቸው። ይህም ማለት በነፃ የሚቀርቡ ልዩ ፍላጎቶቻቸውን የሚያሟሉ አገልግሎቶች እና ድጋፎች ማለት ነው።

**የግለሰባዊ ትምህርት መርሃ ግብር (IEP)**
ይህ ልጁ የሚያገኛቸውን አገልግሎቶች እና የትምህርት አሰጣጥ የሚዘረዝር የጽሁፍ እቅድ ነው።

**አነስተኛ ገዳቢ አካባቢ (LRE)**
ተማሪዎች አካል ጉዳተኛ ካልሆኑ እኩዮቻቸው ጋር በምን ያህል መጠን እንደሚማሩ ያመለክታል።

**ወቅታዊ የትምህርት ስኬት እና የተግባር አፈጻጸም ደረጃዎች (PLAFP):**
የ IEP ግንባታ ክፍሎች። ከበርካታ ምንጮች የተሰበሰበ መረጃ ሲሆን፤ የተማሪዎችን የትምህርት መርሃ ግብር የሚመራ፤ ጥንካሬዎቻቸውን እና ፍላጎቶቻቸውን የሚያንፀባርቅ ነው።

**የልዩ ፍላጎት ትምህርት**
የተማሪዎችን ልዩ ፍላጎቶች ለማሟላት በልዩ ሁኔታ የተነደፈ የትምህርት አሰጣጥ እና ተዛማጅ አገልግሎቶች።





# ለወላጆች የማረጋገጫ ዝርዝር

## ለሚከተሉት ጥያቄዎች "አዎ" ብለው መመለስ ይችላሉ?

የ Marylandን IEP ሂደት መረዳት ከተማሪዎ ትምህርት ቤት ጋር ለሚኖርዎት አጋርነት ወሳኝ ነው። ከታች ካሉት ጥያቄዎች ለአንዱም "አዎ" ብለው መመለስ ካልቻሉ፣ የተማሪዎ ጉዳይ አስተዳዳሪ ወይም የአካባቢ የቤተሰብ ድጋፍ አገልግሎቶች አስተባባሪ ሊረዱዎት ይችላሉ!

### በልዩ ፍላጎት ትምህርት ሂደቱ ላይ

- ❍ በ Maryland ያለውን የልዩ ፍላጎት ትምህርት ሂደት ተረድቻለሁ—ወደ ሚመለከተው አካል መምራትን፣ ግምገማን፣ የ IEP ዝግጅትን፣ የእድገት ሪፖርት አቀራረብን፣ አመታዊ ግምገማን፣ የጊዜ ሰሌዳን፣ የወላጅ መብቶች/ሥርዓት ጥበቃዎችን ጨምሮ?
- ❍ የግምገማ ሂደቱን እና ብቁነት እንዴት እንደሚወሰን ተረድቻለሁ?
- ❍ በግምገማው ሂደት ውስጥ ያለኝን ሚና ተረድቻለሁ?
- ❍ የልጄን ግምገማ በማቀድ ወቅት ስጋቶቼን እና ቅድሚያ የምሰጣቸውን ነገሮች ማካፈል እንደምችል አውቃለሁ?
- ❍ ለግምገማው የጽሁፍ ፍቃድ መስጠት እንዳለብኝ ተረድቻለሁ?
- ❍ ከግምገማው ሂደት በኋላ፤ IEPን በማዳበር ረገድ ያለኝን ሚና ተረድቻለሁ?
- ❍ ልጄ ለምን ብቁ እንደሆነ እና ልጄ ከልዩ ፍላጎት ትምህርት እና ተዛማጅ አገልግሎቶች እንዴት ሊጠቀም እንደሚችል ተረድቻለሁ?
- ❍ ልጄ ለልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት ብቁ ሆኖ ካልተገኘ፤ ለምን እንደሆነ ተረድቻለሁ?
- ❍ ልጄ ለልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎት ብቁ ሆኖ ካልተገኘ፤ አስፈላጊ ከሆነ፤ ለልጄ ምን አይነት ሌሎች አማራጮች ሊኖሩ እንደሚችሉ አውቃለሁ?

### የግለሰባዊ ትምህርት መርሃ-ግብር (IEP)

- ❍ የ IEP ወን ዓላማ ተረድቻለሁ?
- ❍ በ IEP ቡድን ውስጥ ያለኝን ሚና ተረድቻለሁ?
- ❍ IEPን ለማጠናቀቅ እና ለመገምገም ያሉ የጊዜ ገደቦችን አውቃለሁ? በማንኛውም ጊዜ የ IEP ክለሳ መጠየቅ እንደምችል ተረድቻለሁ?
- ❍ የልጄን የ IEP ግቦች፤ እና ግቦቹን ለማሳካት ጥቅም ላይ የሚውለውን በልዩ ሁኔታ የተነደፈ የትምህርት አሰጣጥ እና አገልግሎቶች ተረድቻለሁ?



- ❍ ግቦቹ ልጄ ለኮሌጅ፣ ለማህበረሰብ እና ለስራ ዝግጁ እንዲሆን እንዴት እንደሚያግዙ ተረድቻለሁ?
- ❍ አገልግሎቶቹ መቼ እንደሚጀመሩ፣ በየምን ያህል ጊዜ እና የት እንደሚሰጡ እና ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆዩ አውቃለሁ?
- ❍ አገልግሎቶቹን ለማስጀመር በመጀመሪያው IEP ላይ የጽሁፍ ፈቃድ መስጠት እንዳለብኝ ተረድቻለሁ?
- ❍ ሁሉንም የ IEP አገልግሎቶችን ውድቅ ማድረግ እንደምችል አውቃለሁ?
- ❍ መሻሻል እንዴት እንደሚወሰን አውቃለሁ?

## የወላጅ ተሳትፎ፦ በ IEP ሂደት ውስጥ ሙሉ በሙሉ መሳተፍ

- ❍ በአፍ መፍቻ ቋንቋዬ ወይም እንደ የምልክት ቋንቋ ባሉ የመግባቢያ ዘዴዎች የሚጋራ መረጃ ካስፈለገኝ፤ የአካባቢው የ IEP ቡድን ፍላጎቴን አሟልቷል?
- ❍ ልጄን ከትምህርት ቤቱ ጋር በመተባበር እንዲማር እንዴት እንደምረዳው ተረድቻለሁ?
- ❍ ስለ ልጄ የትምህርት መርሃ-ግብር ስጋት ካለብኝ ምን ማድረግ እንዳለብኝ አውቃለሁ?
- ❍ ስለ ተሟጋችነትና የቤተሰብ ድጋፍ መርሃ-ግብሮች እና እንዴት እነሱን ማግኘት እንደሚቻል አውቃለሁ?
- ❍ ትምህርታዊ መረጃ እንዴት እንደሚጋራ እና የልጄ መዝገብ እንዴት በምስጢር እንደሚያዝ አውቃለሁ?
- ❍ ለልጄ የትምህርት መርሃ-ግብር ጠቃሚ የሆኑ ሰነዶችን እና ማስታወሻዎችን አስቀምጣለሁ? የሚከተሉትን የሚያካትቱ ሰነዶች፦
    - ወቅታዊ እና ያለፉ IEPዎች
    - የሕክምና ግምገማ ሪፖርቶች
    - የግምገማ ሪፖርቶች
    - የወላጅ መብቶች/የሂደት ጥበቃዎች ማስታወቂያ
    - ተፈርመው የተሰራጩ የመረጃ ቅጾች
    - የመምህራን ማስታወሻዎች
    - ከአገልግሎት አቅራቢዎች ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶች
    - ከ IEP ቡድን ስብሰባዎች የተገኙ ማስታወሻዎች
    - በስልክ የተደረጉ ውይይቶች ማስታወሻዎች
- ❍ Maryland ስቴት አቀፍ የቤተሰብ ድጋፍ አገልግሎቶች (FSS) አስተባባሪዎች ትስስር እንዳለው አውቃለሁ? የ FSS አስተባባሪዎች የአካል ጉዳተኛ ልጆች ቤተሰቦችን በሚከተሉት ያግዛሉ፦
    - ስለ ቅድመ ጣልቃ ገብነት እና የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ጥያቄዎችን መመለስ
    - ቤተሰቦች ለሽግግር እቅድ እንዲዘጋጁ ድጋፍ ማድረግ
    - አለመግባባቶችን ስለ መፍታት የበለጠ መረጃ መስጠት

# ጥያቄዎች ካሉኝ ወይም **እርዳታ ቢያስፈልገኝስ?**

## የአካባቢ የቤተሰብ ድጋፍ አገልግሎት አስተባባሪዎች

| የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲዎች | ዕድሜ ከልደት እስከ 5 ዓመት | ዕድሜ ከ 5 እስከ 21 ዓመት |
|---|---|---|
| **Allegany** | 240-920-6829 | 240-920-6829 |
| **Anne Arundel** | 410-562-6303 | 410-424-3258 |
| **Baltimore City** | 410-396-1666 | 443-642-3848 |
| **Baltimore County** | 443-809-9696 | 443-809-5443 |
| **Calvert** | 443-550-8406 | 443-550-8375 |
| **Caroline** | 410-479-3609 | 410-479-3609 |
| **Carroll** | 410-751-3955 | 410-751-3955 |
| **Cecil** | 410-996-5637 | 410-996-5637 |
| **Charles** | 301-934-7456 | 301-934-7456 |
| **Dorchester** | 410-901-6915 | 410-901-6915 |
| **Frederick** | 240-578-1244 | 240-236-8744 |
| **Garrett** | 301-533-0240, x2 | 301-914-1351 |
| **Harford** | 410-273-5579 | 410-273-5579 |
| **Howard** | 410-313-7161 | 410-313-7161 |
| **Kent** | 410-778-5708 | 410-778-5708 |
| **Montgomery** | 240-777-4809 | 240-753-9487 |
| **Prince George's** | 240-521-5054 | 301-431-5675 |
| **Queen Anne's** | 410-556-6103, x10 | 410-758-2403, x135 |
| **Somerset** | 410-651-1616, x11385 | 410-651-1616, x11385 |
| **St. Mary's** | 301-475-5511, x32218 | 240-309-4113 |
| **Talbot** | 410-822-0330 | 410-822-0330 |
| **Washington** | 301-766-8221 | 301-766-8221 |
| **Wicomico** | 410-677-5250 | 410-677-5250 |
| **Worcester** | 410-632-5234 | 410-632-5234 |
| **የ Maryland አይነ ስውራን ትምህርት ቤት** | 410-444-5000, x1489 | |
| **የ Maryland መስማት የተሳናቸው ትምህርት ቤት** | 443-277-8899 | |
| **የ Maryland ስቴት የትምህርት መምሪያ** | 410-767-0255 | |

**የ MARYLAND ስቴት የትምህርት መምሪያ**

**Mohammed Choudhury**
የስቴት ትምህርት ቤቶች የበላይ ተቆጣጣሪ

**Dr. Deann Collins**
የማስተማር እና መማር ቢሮ ምክትል የበላይ ተቆጣጣሪ

**Clarence C. Crawford**
የ Maryland ስቴት የትምህርት ቦርድ፣ ፕሬዝዳንት

**Wes Moore**
አስተዳዳሪ

© 2023 የ Maryland ስቴት የትምህርት መምሪያ
ይህ ህትመት የተዘጋጀው በ Maryland ስቴት የትምህርት መምሪያ፤ የቅድመ ጣልቃ ገብነት ክፍል እና የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ከዩናይትድ ስቴትስ የትምህርት መምሪያ፤ የገንዘብ ድጋፍ #H393A090124A፤ የልዩ ፍላጎት ትምህርት የገንዘብ ድጋፍ ለህፃናት እና ቤተሰቦች “የማገገሚያ የገንዘብ ድጋፎች” በ PL 105-17/111-5 መሰረት የአካል ጉዳተኛ ግለሰቦች የትምህርት ህግ/የአሜሪካ ማገገሚያ እና መልሶ ማልማት ህግ በተገኘ ገንዘብ ድጋፍ ነው። የ Maryland ስቴት የትምህርት መምሪያ፤ የቅድሚያ ጣልቃገብነት ክፍል እና የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች፤ ለ Maryland ሕፃናት እና ታዳጊዎች መርሃ-ግብር መሪ ወኪል ድርጅት ነው፤ በስቴት እና በአካባቢ ኤጀንሲዎች እና ድርጅቶች የተቀናጁ የስቴት አቀፍ የአገልግሎት መርሃ-ግብሮች እና ድጋፎች። በዚህ ህትመት ውስጥ ያለውን መረጃ የሚያባዙ ወይም የሚያጋሩ ተጠቃሚዎች ለ Maryland ስቴት የትምህርት መምሪያ፣ የቅድመ ጣልቃ ገብነት እና የልዩ ፍላጎት ትምህርት አገልግሎቶች ክፍል እውቅና መስጠት አለባቸው፤Dr. Deann Collins፤ የማስተማር እና መማር ቢሮ ምክትል የበላይ ተቆጣጣሪ።



MARYLAND STATE DEPARTMENT OF
EDUCATION
EQUITY AND EXCELLENCE


410-767-0100

www.marylandpublicschools.org

200 West Baltimore Street
Baltimore, MD 21201-2595